# «አንድነት» መድረክን ተቀላቀለ - ከአዉደ ኢትዮጵያ

መጋቢት 2 ቀን 2001

የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኀያሎች ሕብረት (ኢዴኃኅ)፣ የኦሮሞ ፌደራሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን)፣የኦሮሞ ብሄራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ) የሶማሌ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ሶዴኃቅ) እና አረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ሉዓላዊነት በደርጅት ደረጃ፣ አቶ ስዬ አብርሃ የቀድሞ የመከላከያ ሚኒስቴርና ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የቀድሞ የቀደሞ ኢትዮጵያ ፕሬዘዳንት በግለሰብ ደረጃ፣ ማክሰኞ ሰኔ 17 2007 ቀን የመሰረቱትን «መድረክ ለዲሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ ተብሎ የሚታወቀዉን አካል አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) አባል ሆኖ ለመንቀሳቀስ ቅድሜ ጥር 30 ቀን 2001 ዓ.ም የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የላዕላይ ምክር ቤት ባደረገዉ ስብሰባ መወሰኑን ለማወቅ ችለናል።

ኢንጂነር ግዛቸዉ ሽፈራዉ፣ የአንድንት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር፣ አገራችን በፊታችን የሚጠብቃት ከባድ ፈተናን ለመወጣት የኢትዮጵያዉያን በጋራ መሥራት የግድ እንደሆነ አስረድተዉ ገዢዉ ፓርቲ አሁን እያደረገ ያለዉን ለማድረግ የደፋፈረዉ ህዝቡን ተቃዋሚዎችንና የዲሞክራሲ ኃያላትን መከፋፈል በመቻሉ እንጂ አቅምና ጥንካሬ ኖሮት እንዳልሆነም ገልጸዋል።

የአንድነት የሥር አሳፈጻሚዉ አካል ፓርቲዉ «መድረክን» እንዲቀላቀል ከሶስት ሳምንት በፊት ወስኖ የነብረ ሲሆን፣ ላዕላይ ምክር ቤቱ ግን የበለጠ መብራራት ያላባቸው አንዳንድ ነጥቦችን በማንሳትና ዝርዝር መረጃዎች እንዲቀርቡለት በመጠየቅ የሥራ አስፈጻሚዉን አካል ጥያቄ አራዝሞት ነበር። የሥራ አስፈጻሚዉ ኮሚቴ በላዕላይ ምክር ቤቱ የተጠየቁትን አሟልቶ ካቀረበ በኋላ ምክር ቤቱ የሥራ አስፈጻሚዉን ዉሳኔ አጽድቋል።

ከአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በተጨማሪ አገር ዉስጥ የሚንቀሳቀስ የ«ኢትዮጵያ አንድነት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ» የሚባል የፖለቲካ ድርጅት መድረኩን ተቀላቅሏል።

የቀድሞ ቅንጅት አላማና ወራሽ የሆነዉ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ይህን መድረክም መቀላቀል በኢትዮጵያ ፖለቲካ ትልቅ ቦታ የሚሰጠዉና ገዢዉ ፓርቲ ተቃዋሚዎችን የመከፋፈል አቅሙን ከፍኛ እንደሚጎዳዉ ያሳያል የሚሉ የፖለቲካ ተንታኞች ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እንዲፈቱም የአንድነት ፓርቲ እያደረገ ያለዉን ትግል በእጅጉ ያግዘዋል ሲሉ ዜናዉን እንደ ትልቅ አዎንታዊ እርምጃ ይወስዱታል።

መድረኩ የሰብዓዊ መብት በሁለንተናዉ መልኩ እንዲከበር፣ ነጻና ገለልተኛ የፍርድ ስርዓት እንዲገነባና ሕግ የበላይ እንዲሆን፣ እንደ የመናገር የምጻፍ የመደበል ፓርቲ ...የመሳሰሉ ዲሞክራሲያ መብቶች ያለገደብ እንዲከበሩ፣ የግለሰብና የብሄር ብሄረሰቦችን ያካተተ የቡድን መብቶች እንዲከበሩና የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት የተጠበቀ እንዲሆን የሚሉትን አምስት የስብሰቡ መርህዎች ይዞ የሚንቀሳቀስ ነዉ።

መድረኩ ሊያከናዉናቸዉ የዘረጋቸዉም እንቅስቃሴዎች የሚከተሉትን አምስት ግቦች ተግባራዊ በማድረግ ላይ ያተኮሩ ናቸዉ። መድረኩ ሰኔ 17 ባወጣዉ መግለጫ እንደጠቀሰዉ ግቦቹ የሚከተሉት ናቸዉ፡

- በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ በሚንሸራሸሩ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የመድረኩ አባል ድርጅቶችና ግለሰቦች በጋራ የሚስሟሙባቸዉን አቋሞች አንጥሮ ለማዉጣት እንዲያስችል የዉይይት መድረክን ማዘጋጀት
- በኢትዮጵያ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲካሄድ ገዢዉ ፓርቲና መንግስት አመቺ ፖለቲካዊ ምህዳር እንዲፈጥሩ የተባበረ ትግል ማድረግና ለሚቀጥለዉ የ 2002 ዓ.ም አገራዊ ምርጫዎች የጋራ ስልት መንደፍ
- ገዢዉ ፓርቲ ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ወሳኝ በሆኑት በተቃዋሚ ድርጅቶች፣ በአባሎቻቸዉ፣ በሲቪል ማህበረሰቡና ግለሰቦች እንዲሁም በነጻዉ ፕረስ ላይ የሚያደርሰዉን ጫና በሕጉ አግባብ በጋራ ለመመከት
- ለወቅታዊ ሕዝባዊ ሀገራዊ ጥያቀዎች መፍትሄ ለመሻት፣ የጋራ መግለጫዎችን ማዉጣትና ሕዝባዊ የድጋፍ እርምጃዎች በሰላምዊና ሕጋዊ አግባብ ማደራጀትና
- የዲፕሎማሲዉን ሥራ በጋራ መሥራት